# 10ኛ ዓመት

በእድግ ማህበረሰብ ❄ እድግ አቀፍ ትምህርት ቤት ❄

የሽልማት ፕሮግራም

1991-2001

EDEG GENERAL Company!!

ዕድግ አቀፍ ጠቅላላ ንግድ ሥራ አ/ማ

ዕድግ ማለት አንድነት
ዕድግ ማለት ጥበበኛ

EDEG AKEFE GENERAL TRADING S/company

እንኳን ለዛሬዋ ቀን በሰላም አደረሳችሁ ለዚህ ፕሮግራም መሳካት የገንዘብ አስተዋፅኦ ላደረጋችሁ የአ/ማህበር አባላቶችና በጠቅላላ የማህበረሰባችን ተወላጆችን እያመሰገንን ለማህበረሰባችን ሰላም፣ መተሳሰብ፣ ፍቅርና የጋራ እድገት እንመኛለን።

ዕድግ አቀፍ ንግድ ሥራ አ/ማ/
ቦርድ

# የዕድግ ተወላጆች የከፍተኛ ት/ት ምሩቃን ህብረት

ይህን ሕብረት የመመሥረት ሀሳብ የተጠነሰሰው የእድግ አቀፍ የትምህርት ኮሚቴ በ1999 በትምህርታቸው ላቅ ያለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ለመሸለም ባዘጋጀው አመታዊ ዝግጅት ላይ ነው። በዚህ እለት በማህበረሰቡ የተጠነሰሰውን ሀሳብ ተግባራዊ ላማድረግ የትምህርት ኮሚቴው ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የከፍተኛ ት/ት ተመራቂ ተማሪዎች ህብረቱን ለመመስረት በተደጋጋሚ ጥረት ተደርጓል። ምንም እንኳን ጥረቱ አጥጋቢ ውጤት ባያስገኝም በጥቅምት 2001 ይህ ህብረት ተመስርቷል።
በጊዜያዊነትም የሚከተሉት አባላት ተመርጠዋል።

1. ወ/ሮ ፀሐይ መለሰ — በሰብሳቢነት
2. አቶ ያሲን አሊ — በፀሐፊነት
3. አቶ ሙራድ ደሊል — በአባልነት
4. ወ/ት ነኢማ አሊ — በአባልነት
5. ወ/ት ለይላ ኑረዲን — በአባልነት ይዞ ህብረቱ ተመስርቷል።

የማህበሩን መመስረት ለመደገፍና በአባልነት ለመሳተፍ ከኮሚቴ አባላት በተጨማሪ የሚከተሉት ምሩቃን ተገንተዋል።

## የህብረቱ ዓላማዎች

1. የእድግ ተወላጅ የሆኑ ምሩቃን በአንድ ጥላ ስር ማሰባሰብ።
2. በትምህርት ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን እኛ ውጤታማ የሆንበትን መንገድ ማሳየት።
3. ስንማርባቸው የነበሩ የትምህርት መሳሪያዎችን በመፅሐፍ መልክ በማሰባሰብ አሁን በመማር ላይ ላሉ ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን መንገድ ማመቻቸት።
4. ተማሪዎችን ማማከር ለምሳሌ ስለ አጠናን ዘዴ እና ስለ ፊልድ አመራረጥ።
5. ተመርቀው ለወጡት ስለ ሥራ እድሎች ማማከር እንዲሁም ተጨማሪ የትምህርት ስኮላርሽፕ የሚያገኙባቸውን አማራጮች መጠቆም።
6. የተማሪዎችን የእንግሊዝኛ እና የጉራግኛ ቋንቋ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማበረታታት።



7. የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር የችግረኛ ቤተሰብ ተማሪዎችን መርዳት።
8. ምሩቃኑን በማስተባበር ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት።
9. ለተለያዩ የእርዳታ ድርጅቶች ዓላማችንንና ሥራዎቻችንን በማሳየት በገጠር ለሚገኘው ማህበረሰብ የትምህርት፣ የጤናና በአጠቃላይ የመሠረተ-ልማት ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ መፍጠር።
10. ስለተለያዩ የዕድግ የትምህርትና የእድገት ጉዳዮች መወያየት።
11. እንዲሁም በየስራችን ሁኔታ ለምሳሌ በኮንስትራክሽን፣ በዲዛይን፣ በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ በቢዝነስ እና በመሳሰሉት ስራ መደብ ለእድግ ማህበረሰብ ባጠቃላይ እገዛና አገልግሎት መስጠት።

"Youbecome Success If You Win False Friends and True enemies!!" matman

* የትምህርት ሁሉ ዓላማና ግብ ስብዕናን ማዳበር ነው(ፓርከር)
* ትምህርት በፍስህ ዘመን ጌጥ በመከራ ዘመን መጠለያ፣ በእርጅና ዘመን ደግሞ ምርኩዝ ናት። (አርስጣጣሊስ)
* የትውልድ ደረጃ ⇒ልጅ፣ አባት አያት፣ ቅድመአያት፣ ቅም አያት (ቅማያት፣ ቅማንት፣ ቅማት)፣ ድማት፣ ምዝላት፣ አንጅላት፣ ዘር።

## እስካሁን ድረስ የተሸለሙ ተማሪዎች

* በዲግሪ በማስተርና በዶክትሬት ............87
* በዲፕሎም ........................................121
* 12ኛ ክፍል ......................................40
* 10ኛ ክፍል ......................................207
* 8ኛ ክፍል ........................................205

### ገጠር

* 8ኛ ክፍል ..........................................146
* ከ1ኛ—7ኛ ክፍል...............................311



## በ10 ዓመት ውስጥ የተሠሩ ክንውኖች

### 1ኛ ኮሚቴ

- የዕድግ-አቀፍ ትምህርትና ሽልማት ፕሮግራም የሚተዳደርበትን ደንብ አዘጋጅቷል፣
- በከፍተኛ ደረጃ የተቀረፀ ዕድግ አቀፍ የልማት ፕሮግራም ነድፎ ለባህል አስተዳደር ኮሚቴ አቅርቧል፣
- በአቅም ምክንያት ትምህርታቸውን መከታተል ያልቻሉ ተማሪዎችን ረድቷል፣
- የዕድግ ተወላጅ ምሁራን በአገራዊ ጉዳይ ላይ ከምንግዜውም በተሻለ ተቀራርበው አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥረት ተደርጓል።

### 2ኛ ኮሚቴ

- ለገጠር ት/ቤት ውሃ ማስገባት
- ለገጠር ት/ቤት ተጨማሪ ክፍሎች መስራት
- የመማሪያ ዴስኮች ለት/ቤቱ ማበርከት

### 3ኛ ኮሚቴ

- አስረኛውን ዓመት ምክንያት በማድረግ የችግኝ ተከላና ዕደላ ማካሄድ ይህንንም ችግኝ ተከላ በየዓመቱ ለማድረግ ከአብሮ አደግ ት/ት ኮሚቴ ጋር ኃላፊነት መውሰድ፣
- የገጠር ት/ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ለማድረግ ከወሊሶ ወረዳ ተጠሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ
- የእድግ የከፍተኛ ት/ት ተመራቂ ህብረት ጊዜያዊ ኮሚቴ መመስረት

ባሁ ምር ቀበረም እንዴምር ዋረብሁም፣
በሸዋ፣ በአዲስ ከተማ፣ በኮልፌ ቾነሁም
ቢሽርየ መርካቶ ገናሁ ሸበትሁም፣
ዛ የጨነህወ ገን መደረና ባሁም፣
ኤማሽ ሽካከትሁም ቅብሽ የቀባሁ፣
የትምህርት ቤተንዳ ሽመታ ያትረፅሁ፣
የገናሁ ዘንጋሽ ወሬት ቢኸራሁ፣
ነዝሽ ባሰብሁ ዘርማ ይትመናሁ፣
ቲትገደር ቲትረሳ ባሪቅ ይመንእሁ፣
እኳም፣ ነገ፣ ሦስት እባርሁ።

እንዴ ናትባዳነ ይኸር ይኸር ኸማ፣
ቃረዳ አት የኸር ጌታ ይቸንኸማ፣
የትሟኔ ምኑታ ይሽከት ኸማ፣
የትሟኔ ምኑታ ይሽከት ኸማ፣
በስመም ናወርድኔ ናዘልቅኔ ኸማ፣
የገነንዳ ችግር ንዕረፍኔ ኸማ።

ገነዳ ይትረኤ ምኑታ ናብዛነ፣
እንም ንታጠዕነም ተደን ንተሳነ፣
እርስም ንዕመንዳ ቅርስም ታተርፍነ፣
ዜግነት ናኢኔ ባት ንትዋጋነ፣
እኳም ኸረም ነገ ባትነት ንቶትነ፣
ጌታ ንጥብጥነም ፀሎት ናጥብቅነ፣
በገን ይቸን ችግር ያንቄ ንዘብነ፣
ይና ምኑታዳ የምር ናእብነ፣
ይመራንደ ጌታው ጥፏሽ ባንጠበጥነ፣
እንዴ መር ቀበረም ንበነም ንሳነ፣
ትምህርት ቤተዳ ይትረኤ ናስብነ፣



አባናም ጌቤቾ ችግረና ኖድሁ፣
እያ ያሁ ትከ እካ ትንብርሁ።
እያሽ ተትምህርትዌ የጦር ተጣበጥሁም፣
አድግኸ አድግኄ ቦበር አትባቀርሁም፣
አኸሸ አታድጌ ባሁንም፣
ጭዞታ ኸሸረዬ ትኖጥ ላይብረሪ ወርሁም፣
ዛ መፅፍሽ አጠናኤ ብሽን ቂሞታ በከርሁም፣
ኸኋም ተኾርበርሁም የመፃፍ ቤትዌ ምስ ናሜ ባሁንም፣
ቢረብርም ቤርብርም አንጥሁም ተሳርሁም፣
ኤነ ቧርም ቢዩጅን አቻችኸማ ኸርሁም፣
ህሜማ ጠነኤም ኸብርቃር በከርሁም
ህሜማ ጠነኤም ኸብርቃር በከርኩም፣
መፃፍ ተራነሰደም አጠናን ቀበጥኩም።

ዛሽ እያ ወጠሁም ሄታሽ ምር ንበርሁ፣
እያ ያሁ ትከ እካ ትንብርሁ፣
አሁማ ብሰሞ ደናሁ ወረብኹም፣
መቼም የገን ዋስብ ወሬት ይኸራሁ፣
ነዝ ቤቴ ሀነም ቦበር አሳሰብነሁም።

በእድግ አቀፍ ትምህርት ኮሚቴ የገጠር ሽልማት
ፕሮግራም የቀረበ ግጥም

ከተማሪ ምትኬ በቀለ
የካቲት 09 ቀን 2000 ዓ.ም

ትውልድ አገራዊ አገልግሎት በየትኛውም ዘርፍ ሊሰጥ ባለመቻሉ በጣም አሳዝኖናል። የተማረው የማህበረሰባችን አካል ተሰባስቦ የሚተዋወቅበትን፣ ተቀራርቦም በተለያዩ ማህበራዊና ልማታዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርግ ለማስቻል እንዲረዳ የሚያደርግ ጅምር ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በመሆኑም በዚህ ሞራላዊና ሀገራዊ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ የተማረውን ህብረት ክፍል መጠናከር፣ ሙያዊም እገዛ እንዲያደርጉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ስለሆነም እኛ የት/ኮሚቴና የንዑስ ኮሚቴ አባላት ለማህበረሰባችን ዕድገትና ብልፅግና ከማንኛውም ማህበረሰባችን ጋር በጋራ በመስራት ለችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ ለሚደረጉ ጥረቶችና የማህበረሰባችንን ግንኙነቶች ለማጎልበት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከማንኛውም የማህበረሰባችን ጎን ለመቆም ቃል እንገባለን።

በእድግ ማህበረሰብ ውስጥ ልማታዊና ማህበራዊ ስራዎች ለመሥራት የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች የሚሠሩበት የሥራ ዘመን ውስን መሆንና እያንዳንዱ ዜጋ በተለይም የተማረው ክፍል ባገኘው አጋጣሚ በየኮሚቴዎቹ በመሣተፍ ሳይማር ያስተማረውን ወገኑን በከፍተኛ ደረጃ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያገለግለው ይገባል ብለን ስለምናምን ይህንን ተግባራዊ እንድታደርጉ ከአደራ ጭምር ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በመጨረሻም በማህበረሰባችን ተወላጆች ለማህበረሰባችን ከፍተኛ ልማታዊና ማህበራዊ ሥራዎችን የሠሩ ሰዎች በፎቶግራፍ በተደገፈ መረጃ በገጠርም ሆነ በከተማ ማዕከላዊ በሆነ ቦታ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም በጽሕፈት ቤቶች ውስጥ ሊታይ በሚችል ቦታ ሊቀመጥ የሚችልበትን ቦታ ቢመቻች ከላይ የተገለፁት ሰዎችን ለትውልድ የማስቀመጥ ኃላፊነታችንን ልንወጣና የግለሰቦችም ሥራ ታሪክ ሆኖ እንዲቀመጥ ለማድረግ ያስችለናል ብለን እናምናለን።

ፈጣሪ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ሰላምና ብልፅግናን፣ ለማህበረሰባችን ሰላምና ጤና፣ ብልፅግና፣ ፍቅር፣ መከባበርና መተሳሰብን ይስጠን ዘንድ ፈቃዱ ይሁን!!

እድግ አቀፍ ትምህርት ኮሚቴ



## ጌታ አቸናነሁም

አባዳም ጎቤቸም ጌታ አቸነናሁም፣
የገነና ባሁም ሜናሁ ፌታሁም፣
ገናሁ ይትረኤ ቤታሁ ቃሽሁም።
አቸም ይናባሁም ያሁ ወተናሁ፣
እንም ቦሄ ግቦ በትቅየ ቤታሁ፣
ታንበራም አጠፌም ንቅየ ምኑታሁ፣
በንቃር ይከዋሽሽ ስርም ውለታሁ፣
አሁሽ ሰንብቶንደ እንጊ ያስራሁ።

ይናሽ እንም ግዝየ ሂነዳ ይሽርደ፣
ባሁ ይቸን ጥፍወ ያንሳም ያፍካንደ፣
ጠቦጭም ያቸኒ ነሽም ቲይውንደ፣
ጥፎአር ኤንክብሁ አሁሽ እንም ሰንብቶንደ።
እንም ይጎብዜ ህኖሽ ተመኖደም፣
የተማሪ እንም ተብራቶ ባሮደም፣
አባዳም ጎቤቸ አትባደም ሽልማት አቦደም።

ይናም ንስራነሽ ጇዛ ንካስነሽ፣
ገነዳ ንበነም ንትሂታተነሽ፣
ያሁ ቂጭነርም ነትፌነኩሽ፣
ተማሪም የትገና ጌታ የስክትንደሽ፣
ጌታ ባሰናንደ ንትቀበርነኩሽ፣
ጇዛ ንክስነዬ ጌታ ያብቃንደሽ።

## እንኳን ለእድግ ማህበረሰብ 10ኛ ዓመት የተማሪዎችና የላቀ ሥራ የሠሩ ሰዎች ሽልማት ፕሮግራም በሰላም አደረሳችሁ፡፡

ማህበራችን ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ከአብራኩ የወጡትን ተማሪዎችና የላቀ ሥራ የሠሩ ሰዎችን ሲሸልም ከፍተኛ ደስታ የተሰማው መሆኑን ያለፈውና አሁን ያለው የት/ኮሚቴ በሚገባ የሚገነዘብ ሲሆን ተሸላሚዎችም ሆነ በየሽልማቶቹ ላይ የክብር ሽላሚ ሆነው የሚመረጡ ሰዎች በማህበረሰባችን ላይ ያላቸውን ኩራትና ደስታ የሚገልፁበት ቃል እንዳልነበራቸው በየፕሮግራሞቹ ላይ ከሚያሳዩት ስሜት ለመረዳት ይቻል ነበር፡፡

የት/ኮሚቴ ከተመሠረተበት ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ሲያከናውን ካቀዳቸው ዕቅዶች ውስጥ በኮሚቴው አባላትና በተወላጆቹ ጥረት የሽልማቱ ፕሮግራም እስከ አሁን እየቀጠለ ያለና ከሽልማት ፕሮግራሞቹ ውጪ በገጠር ት/ቤት ዙሪያና ልማታዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ ላበረከተው አስተዋጽኦ ባለፈው የሠሩት ሁለቱ የት/ኮሚቴ አባላትና ማህበረሰባችን ከፍተኛ ምስጋና ሊሰጠው ይገባል፡፡

ይህንን ስንል ባለፈው አስር ዓመታት ሊሠሩ ወይንም መሠራት ነበረባቸው ተብለው ከሚታሰቡት ሥራዎች ውስጥ መልካም ሥራ የተሠራ ቢሆንም አመርቂ ግን አይደለም፡፡ በአብዛኛው እቅዶች ላይ የእኛ ማህበረሰብ ግንባርቀደም ይሆንና የሚያስፈልጉ ነገሮች ከተሟሉ በኋላ ወደ ተግባር ለመግባት ሲሞከር ማንኛውም ነገር ከእድግ ማህበረሰብ ባሕላዊ አስተዳደር ኮሚቴ እውቅና ውጪ ማድረግ ስለማይቻል ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ባህላዊ አስተዳደር ኮሚቴ በደብዳቤ ወይንም በአካል ተገኝተው ሲጠየቅ መልስ ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ ሥራውን ለመስራት በሚያስቡ የማኅበረሰቡ ተወላጆች ላይ የሚኖረው ኢሞራላዊ ጫና በቀላል የሚገመት አይሆንም፤ በዚህ ምክንያት ብዙ ጅምሮችም ሆነ ሊጀመሩ የታሰቡ ነገሮች በመሀል ለመቆም ይገደዳሉ፡፡



· እኛ በአሁን ሰዓት ያለን የት/ኮሚቴ አባላትና ለማንኛውም የማህበረሰባችን ተወላጆች ከፍተኛ ክብር የምንሰጥ መሆኑን ከወዲሁ እንዲታወቅልን እየፈለግን በማህበረሰባችን ውስጥ በማህበረሰባዊና በልማታዊ ሥራዎች ላይ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና እንዲሁም ገንዘባቸውን መስዋዕት በማድረግ መስዋዕት ላደረጉና ለሚያደርጉ የማህበረሰባችን ተወላጆች የበለጠ ክብርና ታላቅ ምስጋና መስጠት እንፈልጋለን፡፡

የት/ኮሚቴ ልማታዊ የሆኑ በጎ ሃሳቦችን ወደ ተግባር እንዲለወጡ የሚያደርጉ የማህበረሰባችን ተወላጆችን የሚያበረታታ ሲሆን በማስመሰል ውስጥ ያሉትን ወይንም በጎ በመምሰል ቀርበው ለነገሮች አለመሳካት እንቅፋት የሚያደርጉትን አጥብቆ ይቃወማል፡፡

እድግ-አቀፍ የት/ኮሚቴ አባላት ባሳለፍነው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያትና በሚገጥሙት ሁኔታዎች በማኅበረሰባችን ውስጥ ስለአለው ግንኙነትና ክፍተቶች የተወሰነ ግንዛቤ አግኝቷል ማለት ይቻላል፤ ካገኛቸው ግንዛቤዎች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ያስቀመጠው አጠቃላይ የማሕበረሠባችን ግንኙነት አለመኖር ሲሆን ምንም እንኳን ማህበረሰባችን ከግንዛቤ ማነስ ይሁን በሌላ ምክንያት ጥሪዎችን አለማክበር የተለመደ ባሕል አድርጎ ቢገኝም እንደ ትልቅ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት ግን በማንኛውም አጋጣሚ የሚኖሩ ግንኙነቶች መጨረሻቸው ያማረ ወይንም ውጤታማ ሆኖ አለመጠናቀቅ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ታዲያ ት/ኮሚቴ ለዚህ አብይና ለማህበራዊና ልማታዊ ሥራዎች እንቅፋት የሆነብንን ነገር በምን አይነት ሁኔታ ምን በማድረግ ወደሚፈለገው አስተሳሰብና በጎነት መመለስ ይቻላል ብሎ ጥያቄ ያቀርባል፡፡

አሁን ያለው የት/ኮሚቴ በማህበረሰባችን ውስጥ ያለው የኑሮና የሥራ ዕድገት አበረታችና በተለይም በአሁኑ ጊዜ የሚታየው በጋራ በመሆን እየተመሠረቱ ያሉት አክሲዮን ማህበራቶች ማህበረሰባችን ለሚያደርገው የጋራ ዕድገት ጥሩ ጅምርና ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ቢያምን በአጠቃላይ የተማረው የዕድግ ማህበረሰብ ክፍል ሊያበረክተው የሚችለው ሙያዊና

የአብሮ አደጎች መረዳጃ ማህበር እንደመሥራችነቱ ዕድግ-አቀፍ የትምህርትና ሽልማት ፕሮግራም በቀጣይ ዓመታት ውጤታማ ተግባር እንዲያስመዘግብና የላቀ ደረጃ እንዲደርስ በ10ኛ ዓመታዊ ክብረ በዓሉ ዕለት የመልካም ምኞት መልእክቱን ያስተላልፋል።

ታኅሳስ 26/2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ



## የት/ኮሚቴ የበላይ ጠባቂ

## መልዕክት

እንኳን ለዛሬዋ ቀን በሰላም አደረሳችሁ!

የዛሬ አሥር ዓመት የሽልማት ኮሚቴ ሲቋቋም ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል።

እስከዛሬ የተሠራው ፅንዳለ ሆኖ ለወደፊት ሁሉም የዕድግ ማህበረሰብ በመተባበር በትምህርትና በልማታዊ ሥራዎች የበለጠ እንድንሠራ ጥሪዬን በማክበር አቀርባለሁ።

አቶ አስፋው ተክሌ